# ★ ዴሞክራሲያ ★

* የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ልሳን *

**ዴሞክራሲያ ቅጽ** 37 **ቁጥር** 5 **ግንቦት/ሰኔ** 2004 **ዓ.ም**


## ከሸንብራ ዛፍ ስር ተቀምጠው የሚፈርዱ ዳኞች

ሕዝብ እየተበደለ ፣ እየተከፋ፣ ዋርዶ እየተሰደደ፣ ነፃነት እየጠፋ፣ ሀገር እያወደመ፣ ታሪክና ባኅል እያረከሰ ባለበት ዘመን ፣ ፍትኅ ርትዕ ፣ ዳኝነትና ብያኔ የሚያስተናግዱ ዳኞች ይኖራሉ ተብሎ አይጠበቅም። በሀገርና በሕዝብ ላይ እንዲህ ያለ በደል የሚፈፅመው የአምባገነን ሥርዓት፣ የህግ አውጭውንም ሆነ የህግ ተርጓሚውንና አስተዳደሩን ሁሉ በመዳፉ ጠቅልሎ ራሱ ፈራጅ-ቆራጭ ሆኖ ሕዝብን ቀጥቅጦ ይገዛል። የታሪክም ሆነ የህግ ፣የሕዝብም ሆነ የሞራልና የኅሊና ተጠያቂነት አይኖርበትም። በሀገሪቱ ውስጥ፣ከእርሱ በላይሌላ ልዕል ኃያል ኖሮ ይፈርድብኛል፣ ይቀጣኛል፣ ያባርረኛል ብሎ ስለማይሰጋ የሕዝብ በደል ገንፍሎ በመውጣት እስከተወገደበት ጊዜ ድረስ ያለስጋት ሊቆይ የሚችልበትን ዘዴ ሁሉ ለመጠቀም ይሞክራል። በዚህ አምባገነን ሥርዓት ውስጥ፣ በዳኝነት ተግባር የተመደቡአገልጋዮችና ፍርድ የሚበይኑ ዳኞች፣በሸንብራ ዛፍ ስር ተቀምጠው ፍትኅ-ርትዕ የሚያጠፉ ከአድማስ ባሻገር ለማየት የሚያስችል ኅሊና የሌላቸው ናቸው። የሰውን ልጅ ከእንስሳ ጋር የሚያመሳስለው ደግሞ (ለነገ ትውልድ) የሚያስብ ኅሊና ማጣቱ ነው። ቀደም ሲል የነበሩት ገዥዎች ይህንን ባለማድረጋቸው፣ ይኸው ዛሬ በታሪክና በትውልድ ፊት እየተወቀሱ ይሆኛሉ።

ዛሬ በሀገራች ኢትዮጵያ የሰፈነው ዘረኛ አምባገነን ሥርዓት፣ቀድሞ ከነበሩት አምባገነኖች በበርካታ ሁኔታዎች ከሚለይባቸው መስፈርቶች መካከል አንዱ፣ እጅግ ሲበዛ ጮሌና በሚያስገርምም ደረጃ፣ ቆርጦ ቀጥል የሆነ ውሸታም መሆኑ ነው። በሌላ በኩል ደግሞ፣ ሰኔና ሰኞ ተገጣጥሞልናልና፣ ሁኔታውን እየተጠቀምን ላልተወሰነ ጊዜ መቆየት እንችል ይሆናል ብለው ደምድመዋል። ይህም ሁኔታ ወያኔዎቹ፣ የሀገሪቱን ውስብስብ ችግሮች በርቀት ለማየት የሚያስችል ራዕይ አሳጥቷቸዋል። ብሔራዊ ራዕይን በሩቅ ርቀትለማየት የማይችል ሥርዓትና በሸምብራ ዛፍ ስር ተቀምጦ የሚፈርድ ዳኛ ፣ ተመሳሳይ ባኅርያትና ተግባር ስላላቸው፣ የመጨረሻው እድላቸው ተያይዘው መጥፋት ይሆናል። ታዲያ ዛሬ የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚጨነቀው፣ ስለነርሱ መጥፋት ሳይሆን፣ ትላንት ደርግ ሀገሪቱን አጥፍቶ እርሱም እንደጠፋ ሁሉ፣ ነገም ወያኔዎቹ እነርሱ ጠፍተው ሀገሪቱንም እስከ መጨረሻው እንዳያጠፏት ብቻ ነው። ለዚህ መፃዒ ብሄራዊ ችግር መፍትሄ ለማግኘት ግን፣ በተቃዋሚው ወገን በሚገባ የታሰበበት አይመስልም።ታስቦበት ቢሆንማ ኖሮ፣ እስካሁን አንድ መፍትሄ ሊገኝ በቻለ ነበር። ይህ በሚገባ

ታስቦበት አንድ እልባት እስካላገኘ ድረስ ደግሞ ፣በሀገራችን መጥፋት ፣ማንኛውም ነፍስ ያወቀ የሀገሪቱ ዜጋ ተጠያቂ ልሆን ሮይገባም ለማለት የየሚቻል አይሆንም። ወንጀል ሲፈፀም እየታየ የመከላከል እርምጃ አለመውሰድ ከተጠያቂነት አያድንም። ሌላው ቢቀር ከታሪክና ከትውልድ ወቀሳ ነፃ መሆን አይቻልም። ኢትዮጵያ ሀገራችን፣ ለታሪክና ለትውልድ የሚያስብ ዜጋ እንደማታጣ፣ ኢሕአፓ ሁል ጊዜ ተስፋ ያደርጋል።

ዛሬ የኢትዮጵያ ሕዝብ በረዥም የታሪክ ሂደቱ ባደረገው ጉዞ እንዳሁኑ ያለ ዙሪያው ገደል የሆነ ችግር ገጥሞት አያውቅም ተብሎ ድምዳሜ የተደረሰበት የተለያዩ ምክንያቶች ስለተፈጠሩ ነው።

በመጀመሪያ ደረጃ ይህን ብሄራዊ ጥፋት የሚፈጽመው፣ የባዕድ ኃይል፣ወይም የውጭ ጠላት ወይም ደግሞ የቅኝ ገዥዎች ወራሪ ጦር ሳይሆን፣ በትውልድና በዜግነት/ኢትዮጵያዊ የሆነ ሀገር በቀል የወገን ጠላት መሆኑ ራሱን የቻለ አንደምታ አለው።

ሁለተኛ ይህ ሀገር-በቀል ጠላት፣በዘር ተደራጅቶ በመምጣት ሥልጣን በመጨበጡ የዘረኝነትሥርዓትን ለማስፋፋት የሀገሪቱን የብሔር/ብሔረሰብ ስብጥር በመጠቀም፣ ዜጎችን እየከፋፈለ በማጣላት የሥልጣን ይዞታውን ለማጠናከርና ዕድሜውን ለመራዘም የሚያደርገው እኩይ ተግባር በቀላሉ የሚታይ አይደለም።

ሦስተኛ፣ ይህንን ዘረኛ ሥርዓት የሚቃወምና ከሥልጣኑም እንዲወርድ የሚያደርግ ጠንካራ ተቃዋሚ ኃይል ባለመኖሩ ወያኔ የልብ-ልብ ማግኘቱና ሕዝቡም ሁነኛ የትግል አስተባባሪ ማጣቱ ነው።

አራተኛ፣ ከቀዝቃዛው ጦርነት ፍፃሜ በኋላ የዓለም አቀፍ የፖለቲካ መልከአ-ምድር በመሠረታዊ መልኩ በመለወጡ ምክንያት በሀገሮች መካከል የነበረው የኃይል አሰላለፍ ከፍተኛ መሽጋሸግና ብወዛ ስላደረገ ነው። ይህም ራሱን ችሎ በዲፕሎማቲክና በሀገሮች መካከል በሚኖረው ግንኙነት ላይ ለውጥና አስተጋብዖ አሳድሯሯል። በመሆንም የዛሬይቷ ዓለማችን በአንድ ልዕለ-ኃይል ቀንበር ሥር ወድቃለች። ይህም በመሆኑ፣ በሦስተኛ ዓለም የሚኖሩ ደካማና ደሃ ናቸው የሚባሉት ሀገሮች ለፖለቲካና ለኢኮኖሚ ነፃነት በሚያደርጉት ትግል ላይ ከፍተኛ ጫና አሳድሮባቸዋል። በዚህ ዕውነታ በይበልጥ ተጎጅ የሆኑት ኢትዮጵያና ዜጎቿ ናቸው። በወያኔ ምክንያት፣ የሀገራችን ብሔራዊ ልዕልናም ሆነ፣ የፖለቲካ ነፃነት በባዕዳን እጅ በመውደቁ ምክንያት፣ በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ የወደቀው የሰብዓዊ መብቶች መጣስ፣በደልና ጭቆና፣ እስራትና ግድያ የውጭ ተመልካችና ሀዘኔታ እንዲያገኝ ተደርጓል።

ምንም እንኳን በላይኛው አንቀፅ የተዘረዘሩት ምክንያቶች በአሁኗ ሀገራችን ላይ እንደ ሦስተኛው ዓለም ሀገሮችም ከሞላ-ጎደል ተፅዕኖ ቢያሳድሩም፣ የሀገራችን ዕጣ ፈንታ ግን እጅግ ሲበዛ የከፋ ሆኖ ይገኛል። ለዚህ የከፋ ሁኔታ ሕዝባችን በይበልጥ ሊጋለጥ የበቃውና ከዚህ የችግር ማጥ በቀላሉ፣ ሊወጣ ያልቻለው፣ አሁን በሥልጣን ላይ ያለው የወያኔ ሥርዓት አራማጆች ባኅርይና ተግባር ነው። ይህ ባኅርያቸውና ማንነታቸው፣ የውጭ ባዕዳን በይበልጥ ገላቸውን ሰድደው እንደልባቸው በሀገራችን የውስጥና የውጭ ጉዳይ ገብተው ያሻቸውን እንዲያደርጉ አስችሏቸዋል። ማንም እንደሚያውቀው፣ ምን ጊዜም ቢሆን፣ ምዕራባውያን አጥብቀው

የሚጠሉትና የሚቃወሙት፣ ከቻሉም ሊያስወግዱት የሚፈልጉት፣ በየትኛውም የዓለም ክፍል የሚገኘውን ሀገር ወዳድ መሪ ነው:: ሀገር ወዳድ መሪ ከሆነ፣ ቢከፋም ቢበጅ ፣ የሀገሩን ብሔራዊ ነፃነት ጨርሶ አሳልፎ ስለማይሰጥ፣ የዚያን ሀገር ሀብት የማግኘት ዕድላችን የመነመነ ይሆንብናል ብለው ስለሚገምቱ፣ ምዕራባውያኑ እንዲህ ያለውን መሪ ቢቻል ለማጥፋት ካልሆነ ደግሞ ከማስገልበጥ ወደ ኋላ የሚሉ አይደሉም:: ለዚህም በታሪክ የተደገፈ ማስረጃ ማቅረብ ይቻላል:: ሌላው ቢቀር ከአፍሪካ አህጉር፣ ክዋሚ ንኩርማህንና ፓትሪስ ሉሙምባን ጠቅሶ ማለፍ ይበቃል ::

ዛሬ በሀገራችን የሰፈነውን አምባገነን ሥርዓት የሚያራምዱ ግለሰቦች፣ እንኳንስ ሀገር ወዳዶችና ኢትዮጵያዊ ብሔራዊ ስሜት ያደረባቸው መሆኑ ቀርቶ፣ ነፃ እናወጣሃለን ብለው ለታገሉለት ለትግራይም ሕዝብ እንኳን ቢሆን፣ ፍቅርና ስሜት ያላቸው አይመስሉም:: ያ ባይሆንማ ኖሮ በዘር ላይ የተመሰረተ ከፋፋይ ሥርዓት ዘርግተው፣ በዘመናት ከሌሎች ወገኖቹ ጋር አብሮ በሰላም የኖረውን የትግራይን ሕዝብ ለማቀያየም ባልጣሩ ነበር:: ሀገር ወዳድ መሪ የሀገሩን ብሔራዊ ጥቅም ግን ጨርሶ ለባዕዳን አሳልፎ አይሰጥም:: ይህ ግን በዘመናዊቷ የኢትዮጵያ ታሪክ በሚያሳፍር መልኩ በተግባር የተገለፀው በዘመነ ወያኔ ሆኗል:: ይህ የሀገርን ጥቅም ለባዕድ አሳልፎ የመስጠት አሳፋሪ የክኅደት ተግባር ወያኔዎቹ እንደ ሥልጡን ፖለቲካ ቆጥረውት ሊያኩራራቸው ቢችልም፣ ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ግን አንገት-ሰባሪና አስጠቂ ድርጊት ነው::

በአሁኑ ወቅት፣ የሀገሩ ብሔራዊ ሀብት፣ በባዕድን እየተዘረፈ ከሀገር ሲወጣ እያየ እየሰማ፣ የማይቆጭ፣ የማይበሳጭና ጥቃትና ውርደት የማይሰማው ኢትዮጵያዊ የለም ማለት አይቻልም:: የጊዜ ጉዳይ ነው እንጅ፣ጥቃትና ውርደቱን አስወግዶ፣ የሀገሩን ሉዓላዊነት አስከብሮ ብሔራዊ ሀብቱንና ጥቅሙን የሚያስከብርበት ዕድል እንደሚመጣ ማንም ሀገር ወዳድ ሊጠራጠር አይችልም:: ይህን ዕውን ለማድረግ ግን፣ የኢትዮጵያን የነፃነት ልዕልና የሚያስጠብቅ፣ የሕዝብን ነፃነትና ጥቅም ሊያስከብር የሚችል ነፃ የሆነ ኢትዮያጵዊ መንግሥት መምጣት እንዳለበት ግድ ነው የሚሆነው:: ፀረ-ሕዝብና ፀረ-ሀገር የሆነ ሥርዓትን የሚያራምዱ ግለሰቦች ከምኒልክ ግቢ እስካልተባረሩ ድረስ፣ የሀገራችን ብሔራዊ ሀብት በሰፊው እየተዘረፈ ወደ ውጭ መውጣቱን ይቀጥላል:: የውጭ ባዕዳንም ጥቅማቸውን የሚያስከብርላቸውን ወያኔን አቅፈው-ደግፈው በሥልጣኑ እንዲቆይ ያደርጉታል:: ባጭሩ ለሀገር ጥቅምና ለሕዝብ ነፃነት ደንታ የሌለው ቡድን በኢትዮጵያ ዛሬ መምጣቱ፣ ለውጭ ባዕዳን፣ በተለይም ደግሞ ለምዕራባውያን የማይገኝ ዕድልና ተስማሚ ወቅት ሆኖላቸዋል::

ከዚህ መሠረታዊ ሐቅ በመነሳት ነው ባዕዳን የሀገራችንን ብሔራዊ ሀብት በየፈርጁ ለመዝረፍ ዕድልና አጋጣሚ ያገኙት:: **ለዚህ ሁሉ አደጋ የአጋንንት በረት ሊከፍት የቻለው ደግሞ፣ በምዕራባውያን አቀነባባሪነት፣ የተዘጋጀው የ1983ዓም የሎንዶን ስብሰባ ነበር::** ምዕራባውያኑ፣ በዚህ ስብሰባ እንዲገኙላቸው የፈቀዱት፣ ሦስት ተገንጣይ የብሔር ድርጅቶችን ሲሆን፣ የኢትዮጵያን ብሔራዊ ጥቅም ለማስጠበቅ ሲታገሉ የነበሩትን ድርጅቶችም ይሁኑ ስብስቦች፣ ሌላው ቀርቶ በታዛቢነት እንኳን እንዳይገኙ ከልክለዋል:: የኢትዮጵያን ብሔራዊ ጥቅም

ሊያስከብርና ሊከራከር የሚችል አንዳችም ኢትዮጵያዊ ድርጅት በሌለበትና ኢትዮጵያንም ሊወክል የሚችል ተሳታፊ ባልተገኘበት ጉባዔ የተወሰነው ውሳኔ የህግ ተቀባይነት እንደማይኖረው በውቅቱ የኢትዮጵያ ሕዝብ ተቃውሞውን በታሪክ መዝገብ አስፍሯል፤ አስመዝግቧል:: ኢሕአፓም፣ በበኩሉ፣ በዚህ ፈታኝ ታሪካዊ ወቅት፣ በዚህ አገር አፍራሽ ጉባዔ የተላለፈውን ውሳኔ፣ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጎን ቆሞ ተቃውሞው አብሮ አስፍሯል:: አስመዝግቧል:: ከሸንብራ ዛፍ ስር ተቀምጦ የተላለፈ ፍርድና ውሳኔ ፣ የኢትዮጵያን ኀልውናም ይሆን ልዕልና ሊወስን ከቶ እንደማይችል የኢትዮጵያ ሕዝብ አበክሮ ይገነዘባል:: ታዲያ፣ የባዕዳን አሻንጉሊት ግለሰቦች ዛሬ በሥልጣን ላይ ሆነው ይህን ሁሉ ብሔራዊ ጥፋትና ወንጀል ቢሰሩ የኢትዮጵያ ሕዝብ አይገርመውም:: ትግሉን በመቀጠል፣ የተጠየቀውን ሁሉ መሥዋዕት እየከፈለ ግን የሀገሩን ኀልወና፣ ልዕልና ነፃነትና ብሔራዊ ጥቅሙን የሚያስከብርለትን ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትን ይመሠርታል::

እንዴት? የሚለው ጥያቄ ግን ወቅታዊና አንገብጋቢ እንደሆነ ሁሉም የሚረዳው ሆኗል:: ከሁሉ በፊት ግን ሌላ አንድ ማዕከላዊ ጉዳይ በሚገባ ታይቶ በጋራ ግንዛቤና ዕይታ ውስጥ እንዲገባ ያሻል:: ይኸውም፣ በኢትዮጵያ የፖለቲካ መልከ-ምድር ያለው የኃይሎች አፈረጃጀትና የኃይል ሚዛን ጉዳይ ተገቢውን ዕይታ ሊያገኝ ይገባዋል ብለን እናምናለን:: በዚህ በሀገራችን የፖለቲካ ባኀረ-ዐውድ ውስጥ ሦስት ዋና ዋና ተዋንያን ተሰልፈው ይገኛሉ::

እነርሱም ፦

አንደኛው በወያኔ ዘረኛ አምባገነን አገዛዝ ስር ወድቆ የቁም ስቃዩን የሚያየው መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ነው::

ሁለተኛ የወያኔን አገዛዝ የሚታገለው ክፍል ሲሆን፤

ሦስተኛው ደግሞ በዘር ላይ የተመሰረተን ሥርዓት ያሰፈነው አምባገነን አገዛዝ የኢትዮጵያን ሕዝብ በመከፋፈልና ሀብት በመዝረፍ ላይ የሚገኘው ፀረ አንድነትና ፀረ ዴሞክራሲ ቡድን ነው::

እነኝህን ሦስት ምድቦች በኃይል ሚዛን ሲካተቱ ደግሞ፣ በሁለት አጠቃላይ ጎራ ይሰለፋሉ:: በአንደኛው ሚዛን መላው የኢትዮጵያ ሕዝብና የተቃዋሚው ጎራ ሲሆን ፣ በሌላኛው ጎጥ ደግሞ ወያኔና ተባባሪዎቹ ናቸው:: የትግላችንን አድማስ በማስፋት በነኝህ ሁለት ጎራ የተሰለፉትን ሁለት ተፃራሪ ኃይሎች በቅርብ ስንገመግም፣ ሁለት የማይታረቁ ባላንጣዎች ተፋጥጠው መቆማቸውን እናያለን:: እነርሱም፣ባንድ በኩል፣ ኢትዮጵያ ሀገራችንን፣ ቢቻል ለማጥፋት ካልሆነላቸው ደግሞ፣ ተከፋፍላ በጥቃቅን ጎጣ-ጎጦች እየተከለለች እንድትኖር የሚፈልጉ ባዕዳን ኃይሎችና የዚህ ዕቅዳቸው አስፈፃሚ ያደረጉት ወያኔ ሲሆን፣ በሌላ በኩል ደግሞ፣ መላው የኢትዮጵያ ሕዝብና ዘለዓለማዊት ኢትዮጵያ በዘለዓለም መኖር አለባት ብለው ፀንተው የቆሙ አይበገሬዎቹ የኢትዮጵያ አንድነት ኃይሎች ናቸው:: መላው የኢትዮጵያ ሕዝብና የአንድነት ኃይሎች፣ በማይበገር፣ በማይንበረከክ፣ በማይቸነፍና፣ በማይጠፋ ጎራ ውስጥ መሆናቸውን ያለጥርጥር ማመን ወሳኝ ነው:: ይህንን ለማለት የሚቻለው እንዲያው ለአልኩባይነት ሳይሆን፣

ታሪክ በሚመሰክርለት ማስረጃ ላይ በመመርኮዝ ነው:: ኢሕአፓ የሚከተሉትን ሐቆች ምን ጊዜም ቢሆን በትግሉ አድማስ አስገብቶ ይንቀሳቀሳል:: እነርሱም የእንቅስቃሴው መነሻውና መድረሻው፣ አልፋ-ዖሜጋው ናቸው:: የማንነተነና የዕምነቱ መግለጫዎች ፣ የሰብዕናው መለያዎችና የዜግነቱ መሠረቶች ስለሆኑ የትግሉ መርኖች አድርጎ ያከብራቸዋል:: የእነኝህ ዕውነቶች መሠረቶች የሚከተሉት ናቸው::

1. በጥንታዊቷ ሀገራችን ኢትዮጵያ የዜጎቿ ዕኩልነትና አንድነት መጠበቅ ለጎልውናዋ መሠረት መሆኑ፤
2. የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት መመሥረት ለሀገራችን ዕድገትና ጎልውና ማረጋገጫ ሊሆን እንደሚችል፤
3. በአንድ ሰው አንድ ድመፅ (በሕዝብ ሉዓላዊነት) መሠረት የሚመጣ ሥርዓተ መንግሥት ለሀገር ሉዓላዊነት፣ ለህግ የበላይነትና ለሕዝብ ሥልጣን ዋስትና እንደሚሆን፤
4. ዘርንና ቋንቋን መሠረት ያደረገ ፌዴራላዊ አስተዳደር፣ ለሀገር ዕድገትም ሆነ ለዜጎች አንድነት ዕንቅፋት እንጅ አልሚ እንደማይሆን፤
5. ይልቁንም፣ በሪጅናል ኦቶኖሚ ላይ የተዋቀረ ፌዴራላዊ ሥርዓት - ለዕድገት ግስጋሴ፣ ለአስተዳደርና ለፍርድ አሰጣጥ ቅልጥፍና ስለሚያመች፤ ለሁሉም ዜጋ በየትኛውም የሀገሪቱ ክፍል መንቀሳቀስ የሚያስችለውን ነፃነት ስለሚሰጠው - ተግባራዊ መሆን፤
6. የመድበለ-ፓርቲ ጎልውና፣ ተሳትፎና እንቅስቃሴ የአምባገነን ሥርዓት እንዳይሰፍን መከላከያ መሳሪያ እንደሚሆን፤
7. ከዚህ ጋር ተያይዞም፣ የኢትዮጵያ መንግሥት የሥልጣን ክፍፍል፣ ማለትም፣ የሕግ አውጭው፣ የሕግ ተርጓሚውና አስፈፃሚው ክፍል ተግባር ኃላፊነትና ሥልጣን በሕግ ተለይቶና ተደንብቶ መታወቅ፤ (አምባገነን ገዥዎች ሥልጣን እንዳይዙ ሊከላከል የሚችል በመሆኑ)
8. የሀገሪቱ የበላይ ህግ የኢትዮጵያ ላዕላይ ሕገ-መንግሥት እንደመሆኑ የሕዝብ ነፃነትና ሙሉ ተሳትፎን አግኝቶ በውሳኔ-ሕዝብ መፅደቅ እንዳለበት፤
9. የኢትዮጵያ ሀገራዊ ነፃነት፣ የግዛት አንድነትና ሉዓላዊነት፣ የዜጎቿ ነፃነትና ክብር የማይደፈር፣ የማይገሰስና የማይቀረስ መሆኑን ማረጋገጥ፤
10. ከላይ የተዘረዘሩት መሠረታዊ ጉዳዮች በሀገሪቱ ሕገ-መንግሥት ውስጥ መካተት እንደሚገባቸው ማረጋገጥ፤

እነዚህ አንኳር አንኳር የሆኑ የፓርቲው የትግል መርሆች መሆናቸውን ማመኑ ብቻ ሳይሆን ተግባራዊ እንዲሆኑም ይታገላል::

እነዚህ የፓርቲ ብሔራዊ ራዕዮች በሀገራችን ውስጥ ሥር ሰደው እንዲተከሉና እንዲፀድቁ፣ በተግባርም እንዲተረጎሙ፣ ተመሳሳይ ራዕይና ዓላማ ካላቸው ተቃዋሚ ኃይሎች ጋር ያለመታከት በትጋት ለመሥራት ፓርቲው ምን ጊዜም ዝግጁ ነው።

ይህ ራዕዩን ለማሳካት ግን፣ ከፍ ብሎ በተጠቀሰው አንቀጽ እንደተዘረዘረው ሁሉ ፣ የኢትዮጵያ የፖለቲካ ኃይሎች አሰላለፍ የተስተካከለና የኃይል ሚዛኑም ለሀገራችን ነፃነት ለማስገኘት የሚያስችል አስተማማኝ ኃይል ሆኖ ነጥሮ መውጣት ይገባዋል። ይህንን የኃይል ሚዛን ወደ ኢትዮጵያ የነፃነት ትግል እንዲደፋ ከተፈለገ ደግሞ፣ የተቃዋሚው ክፍል ፣ ቁርጠኛና ወሳኝ የሆነ አስቸኳይ እርምጃ ሊወስድ ይገባዋል። ይህ በየቦታውና በየወቅቱ በቡድን በቡድን እየተሆነ የሚሞከረው የኅብረት ጥረት ሁሉ፣ የተፈለገውን ጠንካራ ሀገራዊ ኅብረት ለማምጣት የማይችል መሆኑን ተገንዝቦ፣ በጋራ ብሔራዊ ዓላማ ላይ የተመሠረተ የአንድነት ኃይል መፍጠር ይዋል-ይደር ሊባል የማይችል አስቸኳይ ሕዝባዊ-ሀገራዊ ጥሪ መሆኑን ማመን አለበት። ከዚህ ውጭ የሚደረገው ሙከራ ሁሉ፣ የሀረግ ሬሳ ተክል፣ ታዛ ፍለጋ ከሚያደርገው ጥረት የተሻለ ውጤት አያስገኝም። ከፋፋይና ጊዜ አጥፊ ከመሆኑም በላይ ለወያኔ ዕድሜ ቀጣይ ከመሆን ያለፈ ፋይዳ አያመጣም። በተጨማሪም " **ተባብራችሁ ከወያኔ ጭቆና ነፃ አውጡኝ** " የሚለውን የኢትዮጵያን ሕዝብ ጥሪና አቤቱታ ሊሰማ ያልቻለ፣ ያልፈቀደ፣ ምላሽ ለመስጠትም ያልተዘጋጀ ነው። ሀገራዊ ጥሪን የማይቀበል፣ ሕዝባዊ ጥያቄን የማይመልስ፣ የሀገሪቱን ወቅታዊ አንገብጋቢ ጉዳዮችን በግምት የማያስገባ ትግል ወጤት አልባ ከመሆንም አልፎ ፣ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ፣ ተወደደም ተጠላ፣ የአምባገነኖች ዕድሜ ቀጣይ ከመሆን አያልፍም።

በኢሕአፓ ዕምነት፣ የሀገራችን ፈርጀ-ብዙና ውስብስብ ችግሮችን በዘለቄታ መልኩ እንዲፈቱ ካስፈለገ፣መላው የሀገሪቱ ዜጎቿን ያሳተፈ፣ ሁሉንም የፖለቲካ ተዋናይ ያስተባበረና፣ ልዩ ልዩ የኅብረተስብ ክፍሎችንም ጭምር ያካተተ ሀገር አቀፍ የሆነ አውደ-መድረክ መዘጋጀት፣ ችግራችንን ለመፍታት የመጀመሪያውና፣ ፈር-ቀዳጅ ምዕራፍ ሊቆጠር ይገባል። ይህ ሂደትና ዝግጅት፣ በሚገባ ታስቦበትና ተመክሮበት ሊጠናቀቅ ግድ ይላል። ሁሉም ዜጋ የሚመኛትን የነገዋን ዴሞክራሲያዊትና ለሁሉም ዜጋ የምትሆን ሀገር ለመገንባት፣ የሁሉም ዜጎቿ ሙሉ ተሳትፎ ወሳኝ ነው። ከዚህ ውጭ የሚደረግ የችኮላና የተናጠል ድካም ሁሉ፣ የባቢሎንን ግንብ ለመስራት ከሚደረግ ከንቱ ልፋት በላይ ሊሄድ አይችልም። አንድን አምባገነን ሥርዓት በማስወገድ ላይ ብቻ ያነጣጠረ ትግል ማካሄድ አንገብጋቢና አጣዳፊ መሆኑ አንድና ሁለት የሚባልበት ጉዳይ አይደለም። በመሆኑም፣ከሁሉም በፊት የቅድሚያ አጀንዳ ሊሆን እንደሚገባው የሁሉም ዕምነት ሊሆን ይገባዋል። ይህ መሠረታዊ ጉዳይ እንዳለ ሆኖ ግን፣የሀገራችን ሁለንተናዊ (ፈርጀ-ብዙ) ችግሮች አምባገነኖች ከተወገዱ በኋላ ወዲያው ይወገዳሉ ብሎ ማሰብ የችግሮቻችንን ጥልቀትና ስፋት፣ ወስብስብነትና አስቸጋሪነት በሚገባ አለመረዳት ይሆናል ብለን እናምናለን።

ከዚህ መሠረታዊ ዕምነት በመነሳት ነው ዛሬ በትግሉ ሂደት፣ ብዙ ተግባራት መጠናቀቅ ይኖርባቸዋል ብለን ሁሉንም የምናሳስበው። ይህን ብርቱ ማሳሰቢያና ማስገንዘቢያ ልናስተላልፍ

የምንሻው፣ ከአለፉት አርባ ዓመታት ከቀሰምነው ተመክሮ በመነሳት ነው። አስቀድሞ ካላሰቡበትና ካልተዘጋጁበት ብሎም ከአድማስ ባሻገር እያሰቡ ካልተሰናዱበት አምባገነን ተክቼ ችግሩን ብቻየን እፈታዋለሁ ቢባል፣ የሀገሪቱ ችግሮች፣ መፈታት ቀርቶ አይቀረፈቱም። የአፄውን ሥርዓት ተክቼ ብቻየን የሀገሪቱን ችግር መፍታት እችላለሁ ብሎ የሕዝብን ሥልጣን የነጠቀው ደርግ፣ በሀገራችን ላይ ያደረሰውን ጠባሳ ሁሉም የሚያውቀው ነው። ወያኔም በፈንታው ከኀልፈተ-ደርግ በኋላ፣ ያደረገው ይህንኑ ነው። የሀገራችን ችግሮች ግን እየባሱ እንጅ እየተሻሉ አልመጡም። ሕዝቡም ከአንድ አምባገነን ሥርዓት ወደ ሌላው የከፋ ሥርዓት ተዳረገ እንጅ፣ ምንም መፍትሄ አላገኘም።

ሥልጣንን በግርግር፣ መንግሥትን በጥሎ ማለፍና በብልጠት አምጥተን፣ የሀገራችንን ችግር እንፈታለን የሚሉ ከንቱዎች፣ ከታሪክ ትምህርት ያልቀሰሙና የኢትዮጵያንም ሕዝብ ማንነትና ምንነት ያላወቁ፣ የሀገሪቱንም ችግር ያልተረዱ በመሆናቸው፣ የኢትዮጵያ ሕዝብ ይታዘባቸዋል እንጅ አያዝንላቸውም። መፃዒ ዕድሉን ግን ማንም እንዲወስንለት አይሻም።

የወደፊቷ ሀገራችን የሚያስፈልጋት ከአድማስ ባሻገር የሚያስቡና ብሔረዊ ራዕይ ያላቸው በሕዝባዊ ሥርዓት ሂደት የሚመጡ መሪዎች እንጅ፣ አዕምሯቸው በጎጥ ክልል የተሸበበ ግለሰቦችና ከሽንብራ ዛፍ ስር ተቀምጠው የመሚፈርዱትን አይደለም።

በሃያ አንደኛው ምዕተ ዓመት ያለችው ሀገራችን ኢትዮጵያ ፍትኀ-ርትዕ የሰፈነባት፣ የሕግ የበላይነት የነገሰባት፣ የዜጎቿ ነፃነት የተከበረባትና በሥርዓተ-ዴሞክራሲ እንድትስተዳደር ስለምንፈልግ ይህ ዕውን እስኪሆን ድርስ ትግላችንን እንቀጥላለን።

ኢትዮጵያ አንድነቷን ጠብቃ ለዘለዓለም ትኖራለች !
ሕዝቧም አቸናፊ ይሆናል !